# "በጋራ ጉዳዮች ላይ የጋራ ርብርብ ለሀገር ልማት እና እድገት "

# STAND AS ONE AND WORK TOGETHER FOR PROSPOURS AND BETTER ETHIOPIA

ከተዘራ አሰጉ

የአንድ ሀገር ህዝቦች በጋራ ጉዳዮች እና በሚስማሙባቸው እሴቶች ላይ በጋራ ተባብረው ለኢኮኖሚ እድገት፤ ለማህበራዊ ሕይወቶች መሳካት ና ለልማት መስፋፋት መነሳሳታቸው ከማንኛውም የበለጠ ሊተኮርበት የሚገባ ጉዳይ ሲሆን ይህ የሀገር እሴት ለሁላችን ታላቅ ተስፋ ሰጪ እና ቸል የማይባል ጉዳይ ነው። ይህን ለመከወን አእምሮአችንን ከተለያዮ አስሮ ሊገድቡን ከሚችሉ ጥቃቅን ስንኮች በመራቅ ልንቀሳቀስበት እና ልንገፋበት ግድ የሚለን ጉዳይ ሲሆን የግል ፍላጎት ሲሳካ ከልብ የሚያስፈነድቀው ሀገራችን አድጋ ምድራችን የሁላችን መናህሪያ እና ያማረች ምድር ሁና ስናያት ብቻ ነው ::

ይህን አምለካከት እና ጽንሰ ሃሳብ አበው አባቶቻችን እና የአለም ታላላቅ ሰወች ሲያስተጋቡት የነበር ከመሆኑ ባሻገር ለዚህ መርህ ሕይወታችውን የሰው አያሌ መሆናቸውን ልንገነዘብ የግድ የሚለን ይሆናል። ሀገር ክፉ ሲያጋጥማት ሆ ብሎ መነሳት የሁሉም በተለይ የኛ ኢትዮጵያዊያን እንደ ባንዴራችን መገልጫችን መሆኑ የቅርብ ጊዜ ትዝታ እና የውረስነው ቅርሰ ሀብታችን ነው ::

ነገር ግን አባቶቻችን እንደወርቅ በነጠረ አባባላቸው ሰላም በተንሰራፋበት ወቅት "ድር ቢያብር አንበሳ ያስር" ማለታቸው ሀይለኛውን ችግር ለማንበርከክ ሳይለያዮ በጋራ ሀብታሙ፣ቀለም የቀጠረው፣ ሰራተኛው፣ ገበሬው እና መላ ሕዝቡ በአንድ ይረባረብ እንደነበር ማንሰላሰሉ የግድ እንዲለን የተቀኙልን ምሳሌያዊ አነጋገር መሆኑን ልንገነዘብ ግድ ይለናል::

ከዚህ በመነሳት መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ውጭ ሀገር ያለውም ሆነ ሀገር ውስጥ ያለው ምድራችን ስትደፈር እምቢ ለሀግሬ ብሎ በጋራ እንድሚነሳ ሁሉ እምቢ ለድህነት በማለት አሁን ያለውን አንጻራዊ ሰላም በመጠቀም አንድ በሚያደረጉን ጉዳዮች ላይ ተሰባስቦ እና ተደራጅቶ መጪውን የኢትዮጵያ ህዳሴ ለማጎልበት ና ለማጠናከር መነሳሳቱ ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ የወቅቱ ጥያቄ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል። ታሪክ እንደሚያሳየን መንግስታት ያልፋሉ ፣ ሰው የተፈጥሮ ግዴታ ነውና ያልፋል ነገር ግን የማያልፍ ነገር ለተተኪው ትውልድ እንደ አባቶታችን ያልውን ነባራዊ ጥቃቅን ልዩነታችንን በማቻቻል እና በመከባበር ተስፋ የሚሰጥ

ሀውልት ተክሎ ለማለፍ በጋራ መነሳሳቱ የአሁኑ ትውልድ እና ሀገሩን የሚውድ ሁሉ ጊዜ ሳይሰጥ ሊሄድበት የሚገባ ጉዳይ ነው ::

ማንኛውም የሕይውት ጉዞ ሆነ ሳይንሳዊ የምርምር ሂደት እንዳሳየን እና እንዳስተማረን የሕዝብን ስሜት፤የጋራ አስተሳሰብ፤ጥቅም እና ፍላጎት አዛምደው ና አቀራኝተው ሳይንሱ እንዲሁም ሳይታጠቁ በግል ራህይ ሆነ በፖለቲካ መነባንብ ግዝፈት በመጥመዝምዝ መባክኑ የራስን ፍላጎት እና አስተሳሰብ እንደማራምድ ይቆጠራል እንጅ የሀገሬውን የጋራ የታሪክ ግኝት ጥቅም እና ፍላጎት አፋፍ እንድማያድርሰው የታየ እና ከሌሎች ካደጉ ሀገሮች ያየነውና እያየንው ያለ ጭብጥ ነው።

ከዚህ ወጣ በለው የሀገርን ጥቅም እና የጋራ አስተሳሰብ ስንቀው እንዲሁም የፖለቲካ ሆነ የግል ራህያቸውን እያዛመዱ የተንቀሳቀሱት ቡዱኖች አንቱ የተባሉ ስራውች እንደሰሩ ልንገነዝብ እና ይህን መካድ ግን አይንን በጨው እንድማጠብ የሚያስቀጥር ይሆናል:: ይህን ጽንሰ ሀሳብ ተንትርሶ የአለም ታላላቅ ሰወችም እንደኛውቹ አያቶቻችን እንዲህ ብልው ከትበውታል፤’’Thus to be independent of public opinion is the first formal condition of achieving any thing great or rational life, or science. Great achievement is assured, how ever, of subsequent recognition and grateful acceptance by public opinion, which in due course will make it one of its own’’ Heiniric Heine, 1797-1856’’

ከዚህ በተጨማሪ የመጻህፍቶች ሁሉ ቁንጮ የሆነው መጽሀፍ ቅዱስ ሆነ ቁረአን መልካም ነገር ስለማድረግ እንዲህ በማለት ሀትቶአል ‘’ be carful to devote themselves all men to what is good. These things are excellent and profitable for every one’’ይህም ማለት መልካም ማድርግ እና ሌሎችን ወደ መልካም መንገድ መምራት ትርፉ ከትርፎቹ ሁሉ የላቀ መሆኑን እያስተማረን ሲሆን ለሀገር ብሔራዊ ጥቅም ሆነ ደህንነት ለጋራ ጉዳይ በጋራ መረባረብ በማንኛውም መልኩ ቢሆን እሰየው የሚያሰኝ ገቢር እንደሆነ እያስተማረንም ነው::

እንዲሁም የጥቂት ሰውችን ሆነ በተለያየ ስም ተደራጂተው የሚንቀሳቅሱ ቡድኖችን ፍላጎት እና ሕልም ብቻ እያሰቡ እና እያራምዱ በአላማ መለያየት ዙረያ አትኩሮ የሀገርን የጋራ ጉዳይ ወደጎን ትቶ መወዛወዙ አዳጋች እና የትም እንደማያደርስ ተቀምጡአል፥፤ ‘’ A little group of will full men representing no opinion but their own; have rendered the countries helpless and contemptible ‘The New York Times.

ከዚህ በመነሳት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ በውጭ ሃገር ያለው ኑዋሪ ሁሉ የተለያየ የአላማ፤ የፖለቲካ እና የአመለካከት ልዩነት ቢኖረንም ከቆምንለት

አላማ ጎን ለጎን ለሀገራችን ሕዝቦች የጋራ ጥቅም ፣ ልማት እና እድገት በደቦ ልንረባረብ የግድ የሚለን መሆኑን የተቀመጠ ሲሆን በዚህ መልኩ ቀና አመለካከት ይዞ በጋራ መንቀሳቀሱ የታላቅነት መለኪያ መሆኑን እንዲህ ብለው ታላቁ ጸሐፊ አስቀምጠውታል ''A constitutional states man in general a man of common opinion and uncommon abilities'' Sir Robert peel::

የፖለቲካ ቡድኖችና ፖለቲከኞች ህርስ በርሳቸው የማያጣጥማችው ጉዳዮች ቢኖርም ሊያስማማችው በሚገባ ብሔራዊ ጥቅሞች ዙሪያ አንድነት በመፍጠር ከሌሎች እንደ ሕንድ ፤ ፓኪስታን ፤ አሜሪካ ፤ እንግሊዝ ፣ ደቡብ አፍሪካ ና መሰል መድበለ ፓርቲ ሀገሮች ልምድ በመቅሰም ቢንቀሳቀሱ ትርፉ የትየለሌ እና የሕዝብን ውስጠ ስሜት የሚያገኙበት ታላቅ መሳሪያ እና የበሳልነታችው መግለጫ መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል ይህን በመንተራስ የወቅቱ ታላላቅ ምሁራን እንዲህ ብለው አስቀምጠውታል '' A politician was a person whose politics you did not agree, when you agree he was a states man''

የኛውቹ አበው አባቶቻችን ከአንድ እናት በተወለዱ ወንድማማቾች እና እህታማማቾች የሚታይን ይህ ነው የማይባል ልዩነት ለመግልጽ ''የእናት ሆድ ዥንጉርጉር'' ቢሉም ተመሳሳይነታቸው ሚዛን እንደሚደፋ በውስጠ ታዋቂነት እያስታከኩ ማስተማራቸው ነው ። '' የሀገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ'' እንዲሁም ''አምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለአምሳ ሰው ግን ጌጡ ነው'' የሚለውን ዘያዊ አነጋገራችውን መቀኘታቸው የሚታዩብንን ጥቃቅን ልዩነቶች በማቻቻል በጋራ ጉዳዮች ላይ ሆ ብለን በአንድነት መነሳቱ ግዙፍ መስሎ የሚታየውን ነገር ሁሉ የሚያቃልል እና በዚህ መልክ ኢምንት የሆነውን የፖለቲካ ሆነ የብሔር ልዩ ነታችን በመከባበር ''unity respecting diversity'' የሚለዉን አገራችን አሁን እየተከተለችው ያለውን አካሔድ በማስረጋጥ ልንቀሳቅስ ይገባል።

ጥንትም ሳይቀር አባቶቻችን ውጤታማ የሚያደርግ ድልድይ መተባበር መሆኑን ልምዳችዉን ተመርኩዘው በሳልነት በተላበሰ መልኩ በዘያዊ አነጋገራች " ድር ቢያብር ኣንበሳ ያስር" Ethiopian proverb: "Enough strands of the spiders' web could tie up a lion." Let each one do his/her part, and cumulatively the difference made will be enormous. በማለት በምሳሌ አስታከው ምክራችውን ጇባ ሰላሉን በጋራ ተባብረን ለሀገር ልማት እና እድገት የመነሻችን ጊዜ አሁን ነው ::

እኛ ኢትዮጵያውያን ሰላማችን እና ድንበራችን በሌላ የውጭ ሀገሮች ተነክቶ የቅርና በክፉ ያነሳትን ሳይቀር በጋራ ማፋጠጥና የምንከራክርላት መሆኑን መናገር ለቀባሪ እንደማርዳት ነው። ነገር ግን አንጻራዊ ሰላም በሰፈነ ወቅት በትንሽ ስንክ መፋተጉን ና መነታረኩን ወደጎን ትተን እንዲሁም በፖለቲካ አላማ ትልቅነት እና ጥልቀት መወዳደሩን ለሕዝብ ዉሳኔ ሰጥተን በጋራ በሚያገናኙን

ጉዳዮች ላይ ነገ ኃብቻ ስናስብ የምንዳርባት ፤ ሲከፋን የምንሸሸግባት ታሪክ ያላት የተሰፋ ምድራችን እምየ ኢትዮጵያ ስለሆነች ለምንወዳት ሀገራችን የታሪክ አሻራ ጥለን ስጋችን ሰላም አግኝታ የምታርፍባት ምድር ትሆን ዘንድ በጋራ ልንረባረብላት ይገባል።

ይህንንም የተቀደሰ ሃሳብ "የዝብሪት ቤት ሳየዘጋ ያድራል" የሚለው ደርሶብን ጠላት እንዳይገባብን ሰላም በሰፈነ ወቅት የሰላም መፊክር አንስተን አገርን በልማት የማሳደግ ትግሉ ላይ እንድንረባረብ ሌሎች ሃገሮች የሀገራቸውን ችግር ተጋፍጠው አሁን ከደረሱበት እድገት የደረሱት ይህን አላማ እና የደቦ ርብርብ አንግበው በመነሳታቸው ስልሆነ እኛ ኢትዮጵያንም አባቶቻችን የሰጡንን አደራ በማተባችን አስረን እና የ ሃያ አንደኛውን ክፍለ ዘመን የእድገት መንገድ ጠራጊ ሃሳብ ይዝን ልንነሳ ይጋባል ።"our researcher into public opinion are content that held the proper opinions for the time of year ; when there was peace ,he was for peace ,when there was war ,he went" 1940 ።

ከላይ የተጠቀሱትን አመለካከቶች የሀገራችን ያለፉት ብልህ መሪውቻችን እንደ አጼ ቴውድሮስ፡አጤ ሚኒሊክ ፤አጤ ዮሐንስ ለሎችም ታላላቅ የስራ መሪወቻችን አሻራ አስቀምጠውልን እና አደራ ሰጠውን አልፋዋል ።

አሁንም ያሉ የአዲሱ ዘመን የኢኮኖሚ እና መልካም አስተዳደር ፊር ቀዳጆች በሳል መሪወቻችን በጋራ ስሩ ፣ ችግር ሲፈጠር በአንድነት ተነሱ በማለት የአንድነትን ጠቃሜታን አስምርው እና አስረግጠው በመስበክ በጋራ እንድንቀሳቀስ እና ለልማት እንድን ነሳሳ አጽንኦት ሰጥተው የተሰፋ ጨላጭል ብሕሊናችን እያበሩልን ነው ።

የአሁኖቹ የተለያዩ የአገራችን የፖለቲካ ፓርቲውች ሆነ መሪወች አንድ በሚያድርጉን ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥተው የሃያ አንደኛውን ክፍለ ዘመን ከፍትጊያ ነጻ የሆነ አህጉር እና አገር የመፍጠር ጭብጥ አለማአቀፋዊ አላማ /Globalization/ በማንገብ ልዩነቶቻቸውን በማቻቻል በጋራ ሊንቀሳቀሱ፤ ሊገፉበት እና ሁላችን ልንነሳሳበት ይገባል::

ይህን መሰረት በማድረግ በውጭ ሃገር የሚገኘው ኢትዮጵያዊ፡ ትውልደ ኢትዮጵያዊ እና የኢትዮጵያ ወዳጆች የሆኑ ሁሉ ውስጣዊ አገራዊ ፍቅር ገፍቶአችው ሊነሳሱ እንደሚጋባ፤ ቁልፍ የሆኑት "Iconic people" የፖለቲካና የግል አስተሳሰባቸውን አቻችለው እና ሊያጋራቸው የሚገባውን የሀገር ቁልፍ ጉዳይ አንግበው ሃሳባቸውን ሆነ ያላችውን እውቀት እንዲሁም ቁሳዊ ሃብታችውን በማፍሰስ በተመቻች እና ሁሉን ባቀራረበ መልኩ ተረባርበው ተጨባጭ የእድገት ፊር ይቀዱ ዘንድ በጋራ ሊነሱ የግድ የሚባልበት ውቅት አሁን ነው ::

የትናትነዋም ሆነ አሁን ያለችው እንዲሁም ለወደፊቱ ታላቅ ሁና ልናያት የምንመኝላት ሀገራችን ሃገር ዉስጥ ያለው ሆነ በውጭ ነዋሪ የሆነው ልቡን ክፍት አድርጎ እና ተቀራርቦ የተሰፋ ሃገሬ ናት የሚላት ኢትዮጵያ በጥቅሉ እምየ ሀገራችን የሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች መናሃሪያ፤ ሰላም የሰፈነባት የምታስቀና እና ኩሩ ማንነታችን ቅርስ ሃብታችን ሆኖ ለዘላለም ይኖር ዘንድ ሁላችን የእምየ ኢትዮጵያ ውጤት መሆናችንን በማመን ጥሩ ህልማችን ይዘን በመነሳት የተሻለች ፤ያማረች እና ጥንካራ ኢትዮጵያን ለመፍጠር በጋራ እንነሳሳ።

ከዝህ በፊት በአባቶቻችን ይታይ የነበረው ፍቅር ፤መረዳዳት፣ መተባብር፣ መከባበር እና የሚያስቀና ዘመን እንደገና እንዲያሰራራ /Renaissance — revival/ ፡ እያ ንሰራራም ስለሆነ ኢትዮጵያ ሀገራችን ብሔራዊ ጥቅሞችዋ መከበሩ የሁላችን ጥቅም እንደተጠብቀ የሚያስቀጠር በመሆኑ የጋራ የሀገራችንን ጥቅም እና ሃብት የማሳደጉ ተልእኮ ነገ ዛሬ ተብሎ ቀጠሮ ሊሰጠው የማይጋባ ጉዳይ ስለሆነ በህልህ እንድንነሳሳ ግድ ይለናል።

ከዚህ አልፎ በህብረተሰቡ ህሊና ዙሪያ የማህበራዊ ግንባታ ስራውችን በመስራት / Social Engineering/ ማለትም ተባብሮ በጋራ ለሃገር መስራት የሚለው ግዙፍ ጽንስ ሃሳብ በሕብረተሰባችን አህምሮ ይሰርጽ ዘንድ የደቦ ስራውን ለመላው ቀና ለሚመኝ ዜጋ በመተው እና ከላይ የተዘረዘሩትን ሰናይ አላማውች ቁንጬ በማድረግ እንድነነሳ አደአ አለብን።

## <u>በሃገራችን ብሔራዊ ጥቅም ዙሪያ በጋራ እና በደቦ መስራት ያለብን ስራውች</u>

1. የአገራችን ገጽታ አሉታዊ በሆነ መልኩ የማስተዋወቅ ስራወችን መስራት እና ማስጠበቅ ፤
2. የአገራችን ገጽታ ሆነ ማንነት በየትኛውም መልኩ ልያጎድፉ ፤ ልያቃልሉ እና በሕልውናዋ ላይ እኩይ አጀንዳ ይዘው የሚንቀሳቀሱ የዉጪ መገናኛ ብዙሃንን ሆነ ተቓአማትን የማረምና የማውግዝ እንዲሁም በዚህ መሰል ስራ እውነታን ሳያገናዝቡ ተባባሪ የሆኑ የዋህ ወግኖቻችንን ታርመው ይመለሱ ዘንድ የምክር ስራ ማከናወን፤
3. የኢንቨስትመንት ስራውች በሃገራችን ተጠናክረው ይቀጥሉ ዘንድ የዉጩን ነዋሪ ማነሳሳት እና የፕሮሞሽን ተግባራትን ማከናወን እንዲሁም በአገራችን ኢንቨስት ያደረጉና እያድረጉ ያሉ ባለሃብቶች ልምዳችውን ሀብታችውን ማፍሰስ ለሚሹ ና ተነሳሽነት እንዲኖር ለመላው እትዮጵያዊ እና ለዉጭ ነዋሪው ኢትዮጵያዊ ልምዳቸውን ኢንድያካፍሉ መድረኮችን ማመቻቸት፤
4. የሃገራችን ብሄር እና ብሄረሰቦች ባሕል፤ወግ እንዲሁም እምቅ ገጽታ የማስተዋወቅ ኢንዲሁም መድረኮችን እና ኤቨንቶችን በማዝጋጀት የባሕል ልውውጥ ከማድረግ ባሻገር በሕዝቦች መካከል የመቀራርብ እና

የግንኙነት አድማስን የማስፋት ስራ መስራት ። በተለይ በውጩ ሀገር ይህ ጉዳይ ትኩረት ተሰጥቶ ሊኬድበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ፤

5. በኢትዮጵያ ፓርላማ ሆነ ውጭ ሆነው በተቃዋሚነት የሚንቀሳቀሱ ፓርቲውች፣ ቡድኖች እና ግለሰቦች ከፓርቲያቸው ፖለቲካ አላማ ባሻገር በሀገራችው የጋራ ብሔራዊ ጥቅም ዙሪያ ተሰባስበው እና ታቃቅፈው በቀና እንዲሳተፉ በተገኘው አጋጣሚ የማሳሰብ ስራ መስራት ፤

6. በሀገር ውስጥ ያሉት ሴት እህቶቻችን እ ና ወጣቶ ች በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን እህቶቻችው እ ና ወንድሞቻቸው ጋር የግንኙነት /Net work/ ፈጥረው የልምድ ልውውጥ እና የመደጋገፍ አካሄድ እንዲፈጥሩ ሁኔትውችን ማመቻቸት ፤

7. በሃገራችን የሚፈጠሩ ሰው ሰራሽ ሆነ የተፈጥሮ አደጋወች ፤ተላላፊ ና የወረርሽኝ በሽታውች ኢንዲሁም ድጋፍ የሚሹ ክስተቶች ሲፋጠሩ ሀገሬውን ሆነ ዉጭ ያለውን ዜጋ በጋራ በማነሳሳት አስፈላጊው ሁሉ ይደርግ ዘንድ መድርኮችን በመፍጠር ድጋፎችን ማሰባሰብ ፡ በልማት ድርጅቶች ሁሉም ኢትዮጵያዊ በጋራ የራሱን ተሳትፎ እንዲያደርግ ሁኔታውችን ማመቻችት ፤

8. በውጭ ንዋሪ የሆነው ኢትዮጵያዊ ሃገር ውስጥ ያሉትን ወንድሞቻችን ና እህቶቻቺን በሀገራቸው ውስጥ ተምረው፤ ሰርተው እና እራሳቸውን አሻሽለው መኖር የመቻል ባህል በአእምሮቸው እንዲሰርጽ ምክር በመቸርና ልምዳቸውን በሃቅ በማካፈል ሃገሪቱ ሃላፊነት የሚቀበል ተተኪ ትውልድ ትፈጥር ዘንድ ሞራላዊ ግደታችውን ይወጡ ዘንድ ሁኔታውችን ማመቻቸት ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር።
በጋራ ለጋራ የሀገር እና የወገን እድገት በደቦ እና በቀና መንቀሳቀስ ትልቁ የእድገት መክፈቻ ቁልፍ ነው።

ተዘራ አሰጉ / ከምድረ እንግሊዝ/